NOTIFICATION OF EL PARTICIPATION
iReady and Developmental Spelling Analysis, Grades 1-6

ውድ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፡

የፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (FCPS) ከ1-6ኛ ክፍል ላሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የiReady ግምገማዎችን እንደ አንድ የአካዳሚክ ሁለንተናዊ ማጣሪያ ይጠቀማሉ። ከiReady ምዘና በተጨማሪ፣ ከ1-6ኛ ክፍል ያሉ ሁሉም የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የቃላት አፃፃፍ እድገት ትንተናን (DSA) ያጠናቅቃሉ።

የiReady ምዘናዎች አላማ በመሠረታዊ የማንበብ እና መፃፍ እና የሂሳብ ችሎታዎች ላይ ክፍተቶች ሊኖራቸው የሚችሉትን ተማሪዎችን መለየት ነው። እንዲሁም የiReady ፈተናዎች የተማሪን የንባብ እና የሂሳብ ችሎታዎች መሻሻል ለመለካት ጥቅም ላይ ይውላሉ። የDSA ዓላማ የፊደል አጻጻፍ ክህሎቶችን እድገትን ለመለካት ነው።

የiReady ግምገማ የንባብ ፈተና እና የሂሳብ ፈተናን ያካትታል። እንዲሁም ከ1-3ኛ ክፍል፣ መምህራን የግዛት ፈተና መስፈርቶችን ለማሟላት የተማሪዎችን የቃል ንባብ ቅልጥፍና ይገመግማሉ። በፈተና ውጤቶች ላይ በመመስረት፣ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ልዩ ችሎታዎችን የበለጠ ለመለየት፤ አንዳንድ ተማሪዎች ተጨማሪ ግምገማዎች ሊፈልጉ ይችላሉ።

ሁሉም ተማሪዎች iReady እና DSA በበልግ/ፎል እና በጸደይ/ስፕሪንግ በየዓመቱ ያጠናቅቃሉ። በበልግ አፈጻጸም ላይ በመመስረት፣ አንድ ተማሪ በክረምት/ዊንተር እንደገና ምዘና ሊወስዱ ይችላሉ። iReady እና DSA የሚቀርቡት በክፍል ውስጥ የመማሪያ ሰዓት ውስጥ ነው። ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ለፈተና የሚሆኑ ቀናትን ይወስናሉ። የተማሪዎ መምህር ወይም የትምህርት ቤት ፈተና አስተባባሪ ለፈተና የታቀዱትን የተወሰኑ ቀናት ያጋራሉ። የiReady and DSA ፈተና አጠቃላይ የጊዜ ሰሌዳ መረጃ በክፍል ደረጃ ፈተናዎች ድረገፅ ማግኘት ይችላሉ። (https://www.fcps.edu/student-assessment/grade-level-tests).

ተጨማሪ መረጃ በiReady ሁለንተናዊ ማጣሪያ ድረገፅ ሊገኝ ይችላል (https://www.fcps.edu/us)። ስለእነዚህ ግምገማዎች ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን የተማሪዎን መምህር ወይም የትምህርት ቤቱን የፈተና አስተባባሪ ያነጋግሩ።